multi cultural communication

Amharic (አማርኛ)
26 January 1998
[BHC-4450]

# የባልና የሚስት ሁከት መላውን ቤተሰብ ይጎዳል
# Domestic violence hurts the whole family

ሴቶች ሰላም ከሰፈነበት ቤታቸው ውጭ መንገድ ላይ ለአደጋ ተጋልጠዋል ብለው የሚያምኑ ከሆነ ተሳስተዋል።

ሴቶች በቤታቸው ውስጥ አብረዋቸው በሚኖሩ ሰዎች የበለጠ ሊጠቁ ይችላሉ። የቤት ውስጥ ብጥብጥ በሁሉም አገር ያሉና በሁሉም የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች ላይ ተፅእኖ ያለው ብዙ ዓይነት መልኮችን የሚይዝ በደል ነው።

ከድብድብ ሌላ ማስፈራራትን፥ ስድብን ወይም የወሲብ ድፍረትን ሊጨምር ይችላል። በሰው የግል ነጻነት ላይ ጣልቃ በመግባት ከቤተሰብ ወይም ከጓደኞች ጋር መለያየት ወይም የሚገባቸውን ገንዘብ ከመስጠት መቆጠብንም ሊጨምር ይችላል። እንደዚህ ዓይነቶቹ በደሎች አንድ የጋራ የሆነ መልክ አላቸው፥ ይሄም አብዛኛውን ጊዜ ወንድ አልፎ አልፎ ሴት ባለቤታቸውን ወይም ሌሎች የቤተሰቡን አባሎች ለመቆጣጠር የሚጠቀሙባቸው መንገዶች ናቸው።

አንዳንድ ሰዎች ይሄ በደል ቤተሰብ ሊከታተለው የሚችል የግል ጉዳይ ነው ብለው ያምናሉ። ነገር ግን በአውስትራሊያ የባልና የሚስት ሁከት ወንጀል ነው። እንዲሁም ቤተሰቦች ከዚህ ድርጊት የሚከላከሉበት መብት አላቸው። በተዘጋ በር ጀርባ በደሉን መደበቅ፥ በደሉ በቤተሰብ አባሎች ሰውነትና አእምሮ ላይ ጉዳት ማድረሱን እንዲቀጥል ይፈቅዳል። ምንም ነገር ካልተደረገ በደሉ አብዛኛውን ጊዜ በጣም መጥፎ ይሆናል፥ አንዳንድ ጊዜም ውጤቱ ሞትና አሳሳቢ የሆነ የሰውነት ጉዳት ይሆናል።

ምንም እንኳ አንድ ሰው፥ አብዛኛውን ጊዜ የወንዱ ባለቤት የበደሉ ኢላማ ብትሆንም፥ በደሉ መላው ቤተሰብ ላይ ተጽእኖ አለው። በደል በሚፈጽሙ ቤተሰቦች ውስጥ የሚያድጉ ልጆች ራሳቸው ችግር ሊኖርባቸው ይችል ይሆናል፥ ትልልቅ ሰዎችን በተለይም ወንዶችን ማመን አይቻልም ብለው ሊያስቡ ይችሉ ይሆናል፥ የመጠጥና የሱስ ችግሮችም ሊኖርባቸው ይችል ይሆናል። ሲያድጉና የራሳቸው ባላቤትና ልጆች ሲኖራቸው፥ እነሱም ላይ በደል ሊፈጽሙ ይችሉ ይሆናል። ስለዚህም ነው የባልና ሚስት ሁከት ማንም አያገባውም ማለት የማንችለው፥ መላው ሕብረተሰብ ላይ ተእጽኖ አለውና።

ቡብዛት የሚቆጠሩ ሴቶች የባልና የሚስት ሁከትን ለብዙ ዓመታት ችለው ይኖራሉ። አንዳንድ ጊዜም "ይገባኛል" ብለው ስለሚያምኑ ነው ወይም በሌላ ምክኒያቶች እንደ ቁማር ፥ መጠጥ ወይም የፍቅር ግኑኝነት ችግሮች ናቸው ብለው በይቅርታ ያልፉታል። ነገር ግን ማንኛውም ሰው እንደዚህ አይነት በደል ሊፈጽምበት አይገባም ስለዚህም በምንም ማመካኘት አይቻልም።

ሴቶች እንዴት ነው እራሳቸውንና ልጆችቸውን ከባል ሁከት የሚከላከሉት? የምክር፥ የሕግ ምክር ወይም ለድንገተኛ ጊዜ የሚሆን መኖሪያ የሚሰጡ የርዳታ አገልግሎቶች አሉ። ሃኪም (GP)፥ የአካባቢዎ የሕክምና ጣቢያ ወይም የሴቶች የሕክምና ጣቢያ ከላይ ከተጠቀሱት አገልግሎቶች ጋር ያገናኙዎታል። የባልና የሚስት ሁከት (Domestic Violence) ልዩ መስመር 1800 65 64 63 በመደወል መረጃ ሊያገኙ ይችላሉ። በእንግሊዝኛ መግባባት ከአስቸገርዎ የአስተርጓሚ አገልግሎት (Interpreting Service) 13 14 50 ስልክ እንዲደውሉ ሊረዳዎ ይችላል። ሴቷ ለመለያየት ከወሰነች የሕግ እርዳታ ሊያስፈልጋት ይችላል፥ የሁከት ማቆሚያ ትእዛዝ (AVO - Apprehended Violence Order) ለማግኘት እርዳታ ያስፈልጋት ይሆናል።

ይሄም ወንድ ባለቤቱ ላይ ጥቃት እንዳያደርስ፥ እንዳስፈራራ ወይም ዛቻ እንዳያበዛ ማስጠንቀቂያ የሚሆን ሕግን የተከተለ መንገድ ነው። ትእዛዙን የማያከብር ከሆነ በፖሊስ ሊታሰር ይችላል።

የሕግ ምክርና ኤቪኦ (AVO) ን እንዲያገኙ የሚረዳ በቻምበር ማጅስትሬት (Chamber Magistrate) ፍርድ ቤት (local court) ውስጥ ይገኛል። አንዳንድ ፍርድ ቤቶችም እንግሊዝኛ ትንሽ ትንሽ ለሚናገሩ ወይም እንግሊዝኛ ጭራሹን ለማይናገሩ ሰዎች፥ ለሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሠራተኞች ወይም አስተርጓሚዎች የሚጠቅም የባልና ሚስት ሁከት እርዳታ ማግኘት የሚችሉብትን መንገድ የያዘ እቅድ አላቸው። እርዳታ መፈለግ አስቸጋሪ ውሳኔ ሊሆን ይችላል፥ ነገር ግን ለቤተሰቡ ሰላም መጀመሪያ የሚወሰደው እርምጃ ነው።

የባልና ሚስት ሁከትያጋጠማቸው ሰዎች ጓደኞችና ዘመዶችም ይሄን በተመለከተ እርዳታ ሊያደርጉ ይችላሉ። ይሄም ማለት ሴቷ "ኢጋና እንድትናገር" ወይም "ለሰውየው የበለጠ ትዕግስት እንዲኖራት" ወይም "ነገሩን የበለጠ እንድታከር" ለማድረግ ሳይሆን፥ እሷ በምትለው በማመንና እርዳታን በማድረግ ነው። ማኅበረሰቡም የባልና የሚስት ሁከት ተቀባይነት የለውም በማለት ተቃውሞውን በማሰማት ሊረዳ ይችላል።

በእንግሊዝኛ ስልክ ለመደወል እርዳታ ከፈለጉ የአስተርጓሚ አገልግሎትን (Translating and Interpreting Service - TIS) በ 131 450 ይደውሉ።

በርካታ የጤና ነክ መረጃዎችን (health information) በቋንቋዎ ከብሔረሰቦች መገናኛ (Multicultural Communication) ዌብ ሳይት (website) ላይ http://mhcs.health.nsw.gov.au ሊያገኙ ይችላሉ።

የስልክ ቁጥሮች ይህ ጽሑፍ እስከታተመበት ጊዜ ድረስ ትክክለኛ ናቸው፥ ነገር ግን በተከታታይ ለውጥ ሲኖር አይቀየሩም። ስለዚህ የስልክ ቁጥሮችን በስልክ ማውጫ ላይ እንገደና ማየት ሊኖርብዎት ይችላል።

REVIEWED
April 2003
NSWMulticulturalHealthCommunicationService